# የሕዝቡ አደራ ይከበር

**ሚካኤል ተፈሪ 11/27/12**

አደራ ማስጠትና መቀበል በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለመደ ክንውን ነው። አደራ የሚሰጠው ሰው ድርጅት፣ ፓርቲ፣ መንግሥት፣ በታማኝነቱ፣ በሥነ ምግባሩ፣ በቃል አክባሪነቱ አንቱ የተባለ መሆኑ ተረጋግጦ ነው።

በአጋጣሚ በሆይ ሆይታ በችኮላ የተሰጠ አደራ ኋላ ላይ እንደተጠበቀው ሆኖ ካልተገኘ በኅብረተሰቡ ዘንድ የሚያሰጠው ቦታ ከዝቅተኛም በታች ዝቅተኛ ነው።

አደራ በሊታ ለዋስትና አይበቃም፤ ለትዳር አይመረጥም፤ ለሽምግልና አይጋበዝም፤ በማህበር የክብር ቦታ አይሰጠውም፤ በእድር፣ በደቦ፣ ለሚዜነት ቦታ አይታጭም። ይህ የቆየ የኢትዮጵያውያን ባህል ነው።

አደራ አክባሪ ይከበራል፣ ሽማ ተደርቦለት የፊት ረድፉን እንዲሜራ ይጋባዛል፣ ይመረቃል፣ ያስማማል፣ ያስታርቃል በኅብረተሰቡም ሆነ በመንግሥት ደረጃ የክብር ሥፍራን ያገኛል።

ታዲያ አደራው ከግለሰብ አልፎ የሕዝብ አደራ ከሆነ ሸክሙ ከበድ ይላል። ራስን ካላወቁ፣ የሚሰሩትን ነገር ካልተገነዘቡ፣ ሕዝብን ካልናቁ በስተቀር ከኅብረተሰቡ የተቀበሉትን አደራ የትም አራግፈው ሜዳ ዳፋው በቀላሉ የሚጥሉት ዓይነት አይደለም።

መኖሪያ ቤቴ ከቀበሌ ጽህፈት ቤት መቶ ሜትር ብርቅ ነው። እንደ ሁልጊዜው በማለዳ ተነስቼ ቁርሴን ከበላላሁ በኋላ የግቢዬን በር ከፍቼ ስወጣ የተማለከትኩት ረዥም ሠልፍ፣ የሕዝቡ ሥርዓት አክባሪነትና ተነሳሽነት ምንጊዜም ከወስጤ አይጠፉም።

1997 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ መንግሥታትና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እኩል ተቀምጠው ልንመራው እንፈልጋለን ለሚሉት ሕዝብ አማራጫቸውን ያቀረቡበት በነፃነት ጓዳ ጎድጓዳ ቦታ ሳይቀር በመግባት የቀሰቀሱበት የምርጫ ዘመን።

ኢህአዴግ በምርጫ ማሳተፍና ለሕዝቦች ፈቃደኝነትና አደራ ሰጪነት አገሪቱን ማስተዳደር ከጀመረ ሁለት ሰባት ዓመታትን ያሳለፈ ቢሆንም አመራሩና አባላቱ የምርጫውን ሥነ ምግባር ከምንጊዜውም በተሻለ ሁኔታ በማክበር እንዲንቀሳቀሱ ሥልጠና ከማስጠት ባሻገር ሥነ ምግባሩን ለማያከብሩት አባላቱ ላይ የማያወላውል የሥነ ምግባር እርምጃ ለመውሰድ የተንቀሳቀሰበት የምርጫ ዘመን።

በአንዳንድ ተቃዋሚዎች በኩል ደግሞ ፊት ለፊት የሠላም ካባ በመልበስ አፈ ጮሌነታቸውን ያሳዩበት፣ በድብቅ ኢህአዴግን የሚጠ ወሻ ይወለድ የሚል መዛላ በማስመሰል የዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሥነ ምግባርን የጣሱበት የምርጫ ዘመን።

ምርጫ ሕዝቦች፣ ቡድኖች፣ ግለሰቦች፣ ጥቅማችንን ሊያስከብርልን ይችላል ብለው ለሚያምኑበት ፓርቲ ድምፄ በማስጠት አደራቸውን የሚያስተላልፉበት ሥልት ነው። ለዚህ ነው ሕዝቡ የሚጠው ፓርቲ ሥልጣን ሲይዝ የገባውን ቃል፣ የተረከበውን አደራ በተግባር እንዲያውል የሚጠየቀው።

የተናገሩት ከሚጠሩ የወለዱት ይጥፉ ይል የለ የአገሬ ሰው። ወደቀደመው ትውስታዬ ልማስስና ያ ሞቅ ደመቅ ብሎ የተጀመረው የምርጫ ቅስቀሳ ነበር የሕዝቡን ሥነ ልቦና ገዝቶ ከጠዋቱ 12.00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4.00 ሰዓት እንዲሰለፍና ድምፁን እንዲሰጥ አደራውን እንዲያስተላልፍ ያስቻለው።

መንግሥት ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመሆን ያቋቋመው የምርጫ ቦርድ ተግባሩን በትክክል እንደሚወጣ ሕዝቡ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ አልነበረውም።

በየትኛውም አገር እንደሚደረገው ቦርዱ ወጤቱን በይፋ ሲገልፅ ተሸናፊው ለአሸናፊው እንኳን ደስ አለህ በማለት በሰለጠነ አኳኋን አብረው ለአገር ልማት እንደሚቆሙ አብረው እንደሚሰሩ ለማዳመጥ ነበር ፍላጎቱ – የሆነው ግን ሌላ ነው።

ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ አዲስ አበባ ላይ ምርጫ በማጭበርበር እንዳሸነፈ ለሚዲያ ቃል ሰጡ። ከምንጊዜውም በላይ የአገሪቱን ገፅታ ሊቀይር በሚችለው የምርጫ ቦርድን ቃል ሲጠበቅ በነበረው ሕዝብ ላይ ወሻባንብር ነዞበት።

የሆነው ግን ሌላ ነው። ምርጫ ቦርድ የገለፀው ወጤት ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ሚልኩ አዲስ አበባ ላይ ተቃዋሚዎች ማሸነፋቸውን ሕዝቡ አደራውን አስተላልፎ እንደሰጣቸው ነው።

የሕዝብ አደራ፣ በድንገት እጅ የገባ አደራ፣ የተደራጀ አቅም ያለው፣ የጠራ የፖለቲካ ማስመር የሚከተል ቁልጭ ያለ የፓርቲ ፕሮግራም መንግሥት ቢሆን፣ ከተማ አስተዳደር ቢሆን፣ ክልል ቢያስተዳድር እሚራብታለሁ የሚለው ፖሊሲና የሚከተለው ስትራቴጂ ያለው ፓርቲ የሕዝቡን አደራ ተቀብሎ የገባውን ቃል ለሚፈፅም ወደ ኋላ እንደሚዬል ከብዙ አገሮች እና ከኢህአዴግ አይተናል።

በተቃዋሚዎች በኩል የታየው ግን ሌላ ነው። ሕዝቡ እንዲመራቸው ማጠየቅ፣ በስብሰባ አዲስ አበባን እንረከብ አንረከብ በማለት ሕዝብን ቁም ስቅል ማስጣት እኔ የማውቀው ፓርቲ ሕዝብን ሲመራ ነው። ሕዝቡ በፓርቲው አጀንዳ ዙሪያ በማስብሰብ ለተግባራዊነቱ ሲንቀሳቀስ ነው።

ኢህአዴግ ያሳየንና ከሌሎች አገሮች የተማርነውም ቢሆን ይህንን አካሄድ ነው። አቅሙ ሲጠፋ፣ ቁርጠኝነቱ ሲያንስ የወስጥ የሥልጣን ሽኩቻ አላሳርፍ ሲል ጀቡ ላይ ሆኖ ከታች ወኃ የምትጠጣውን አህያ ለምን ታደፈርሺብኛለሽ እንዳለው ዓይነት ነገር ፍለጋ ወስጥ ነው የተገባው።

የህዝብ አደራን አሽቀንጥሮ ወደመጣል ነው የተደረሰው። ለዚህ ነው ህዝቡ ተቃዋሚዎችን አደራ በሊታ የሚል ታርጋ የለጠፈላቸው።

እንኳን አገር ዕድር ለማምራት አቅም የላችሁም እያላቸው ያለው። ተቃወሞ አማራጭ ሀሳብን በማቅረብ የተደራጀ የፓርቲ አወቃቀርን በማከተል ከተሚጡ አገርና ህዝብን ለማገልገል ነው።

ካልተሚጠም የገዠዉን ፓርቲ እንከን በማውጣት እንዲያስተካክል የህዝብ ድምፅ በማሆን በተገኘው ሜድረክ ላይ ሚከማትን ለአገር በሚጠቅም ፖሊሲ ዙሪያ አባሎቻቸዉንና ሌላዉንም ዜጋ በማንቀሳቀስና በሚደራጀት ለተፈፃሚነቱ መቆምን ይጠይቃል።

ከ1997 ዓ.ም ምርጫ የተረዳነው ህዝቡም የተማረው የተደራጀ፣ በአግባቡ የተተነተነ በሁሉም ማስክ አገርንና ህዝብን ለለወጥ የሚችል ፖሊሲና ስትራቴጂ ሳይዙ ለምርጫ በመቅረብ በአፈጮጣት ምረጡን የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች አደራ መቀበል ያለመቻላቸዉን ነው።

በአግባቡ የተደራጀ ፕሮግራም፣ አገርን የሚያስተዳድርበት ፖሊሲና ስትራቴጂ ያለው ፓርቲ ህዝቡ የሰጠዉን አደራ በመቀበል በዕድገት ላይ ዕድገት እያስማዝገበ የገባዉን ቃል በተግባር መተርጎሙን ነው። ለዚህ አባባል ኢህአዴግ ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያን በመምራት ያስማዝገበው ውጤት በቂ ማስረጃ ነው።

የህዝቡ አማካከት ተለውጧል። ባዶ ተስፋ፣ ጩኸትና ሮሮ፣ አትነሳም ወይ የሚሉ ሜኪክር ባዶ ቅዠት ዳቦ እንደማይሆን ተረድቷል። የአገርን ገፅታ እንደማይቀይር ተገንዝቧል።

ዕድገትና ብልፅግና ሰላምና ዴሞክራሲን እንደሚያስገኝለት አወቋል። ለዚህ ነው በተግባር ተፈትኖ ላለፈው ኢህአዴግ በምርጫ 2002 በነቂስ በመውጣት እንዲመራው አደራዉን የሰጠው።

ኢትዮጵያ በሁሉም ማስክ ተቀይራለች፣ አድጋለች፣ ወደ ብልፅግና ጉዞ ጀምራለች። ይህን ለማስቀጠል ለህዝቡ የተሰጠ ብቸኛው አማራጭ ነው። ዘንድሮ በሚደረገው ክልላዊና ሀገር አቀፍ ምርጫ እንደ ከዚህ ቀደሙ በነቂስ ወጥቶ ዴሞክራሲያዊ መብቱን እንደሚጠቀም ጥርጥር የለኝም።

ዛሬ ዓለማችን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዕድገት በማጠቀም ወደ ማንደርነት የተለወጠችበት ወቅት ላይ ነው የምንገኘው። አወሮፓና አሜሪካ ወስጥ እየተከሰቱ ያሉ ለወጦችን በየቀኑ እየተከታተልን ነው።

የአገራቸዉን ኢኮኖሚ ማስደግ ያልቻሉ፤ የህዝቡን ኑሮ መቀየር ያዳገታቸው፤ ኢኮኖሚ በየጊዜው ከሚቀያየረው የዓለም ፖለቲካል ኢኮኖሚ ጋር አብረው መጓዝ ያልቻሉ ፓርቲዎችን ሜሪዎች የህዝቦችን ፍላጎት በመቀበል ስልጣናቸዉን ለተቃዋሚዎች እያስረከቡ ነው።

ከደቀቀ የምጣኔ ሀብት ጉዞ አገርንና ህዝብን ሊያላቅቅ የሚችል ፖሊሲና ስትራቴጂ በማዘጋጀት ህዝብን አስተባብረው በዕድገት ላይ ዕድገት እያስማዝገቡ ያሉ ፓርቲዎችና አሜራሩ በርቱ ተበራቱ ከጎናችሁ ነን የሚሉ የህዝባቸዉን ድምፅ፣ እያገኙ ነው።

የአለም ህዝብ የሚፈልገው ሰላምን፣ ዴሞክራሲንና ልማትን ነው። እኛም እንደ አገር የምንፈልገዉና የምንመኘው ይህንኑ ነው። ለዚህ ነው ተግባርን ማዕከል አድርገን የዓለም ተጨባጭ ሁኔታን ተገንዝበን ለምርጫ በንቃት ማዘጋጀት ይኖርብናል የምንለው።

አገሪቱ በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ዕድገት ላይ እየተራመደች መሆኑ ግልፅ ነው። ዕድገቱን ለማስቀጠል የአገሪቱን ገፅታ አሁን ካለው በተሻለ ለዓለም ህዝብ ለማሳየት በምርጫው መሳተፍ የግድ ይለናል።

ወቅቱ ወዳጅና ዘመድ የሚለይበት ነው። እንደ ከዚህ ቀደሙ ምርጫ አፈ ጮሌነት ቦታ የለውም። ያረጀ ያፈጀ ውሃ የማይቋጥር አጀንዳ ይዞ መቅረብም ጊዜ ማጥፋት ነው።

ህዝቡን በሶስት ሺህ ዓመታት የነፃነት ታሪክ ትረካ ማዝናናት የተበላ ዕቁብ ዓይነት ነው። ምክንያቱም የአገር ነፃነት ብቻውን ከምጣኔ ሀብት ባርነት ነፃ እንደማያወጣ ተረድቶታልና። ወደብ፣ የባህሪ በር የነበራትና ብዙዎች ህይወታቸውን ያጠፉበት፤ አካላቸው የጎደለበት፤ ነፃነት የምጣኔ ሀብት ባርነት ነፃ እንዳልወጣን ተረድተዋልና፡፡

ኢትዮጵያዊነት የሀገር ፍቅር፣ የሚሉ የተዋቡ ቃላት ለገዢዎችና ለጥቅም ተካፋዮቻቸው ወፍራም የብልፅግናና የድሎት ሸማ፤ ለአገሪቱ ብሔር፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የባርነትና የድህነት ማለሜ እንደ ነበሩ በግልፅ ገብቶታልና የራስን ዕድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የምትለው አንቀፅ 39 ኢትዮጵያን ለማከፋፈል፤ ህዝቧን ለማበተንና እርስ በርስ ለማባላት የተቀመጠች አንቀፅ ያለመሆኗን ህዝቡ በተጨባጭ አረጋግጧል።

የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ህገ መንግስቱ በፈቀደላቸው መብት ተጠቅመው ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ያሳዩት ማበታተን፣ እርስ በርስ መፋጀት፣ መገነጣጠልን አይደለም።

እንዲያውም ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው በማስተዳደራቸው፣ ከአገሪቱ ሀብት እኩል ተጠቃሚ በመሆናቸው ቋንቋቸውን፣ ባህላቸውንና ሃይማኖታቸውን በነፃነት በማልገላቸው፣ በማስፋፋታቸው ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሜልኩ ነው ኢትዮጵያዊነትን በተግባ ያረጋገጡት።

ለሀገራቸው ያላቸውን ፍቅር ማስዋዕት እስከ መሆን ድረስ ነው የገለፁት። ትናንት እንደ ኢትዮጵያዊ የማይቆጠሩ ሁልጊዜ በጥርጣሬ ዓይን ሲታዩ የጦርነት ምንጭ

የነበሩ አካባቢዎች ሳይቀሩ ነው አንገታቸውን ቀና አድርገው በሙሉ ልብ ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚገልፁት።

ታዲያ መንግስትና ህዝብ በጊዜ የለንም መርህ የተጀመረውን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ግቡን እንዲመታ በሚረባረቡበት ወቅት ያረጀ ያፈጀ አጀንዳ ይዞ ህዝቡን ሚደናቀር የራስ መደንቀርን ያሳያልና ጠቃሚ አጀንዳ ማዘጋጀቱ የሚጠቅም ይመስለኛል።

ጊዜው የስራ ነው። የተግባር ጊዜ ነው። ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ ጊዜ ነው። መስማማትን መተባበርን ልዩነትን ይዞ በአንድነት ማለፍን የሚጠይቅ ወቅት ነው ያለነው። በከፍተኛ ወድድር ወስጥ ባለች ዓለም።

ህዝቡ የሚፈልገው ለራስ የተመቻቸ ኑሮ ወቅቱ ያመጣውን አጀንዳ ሁሉ እየያዙ የሚያስተጋቡ ፓርቲዎችን ሳይሆን ለአገር ዕድገት ሌት ተቀን የሚተጉ የረጅም ጊዜና የአጭር ጊዜ የዕድገት ፕሮግራም ራዕይ፣ ፅናትና ብርታት፣ ራስን ማስዋዕት እስከ ማድረግ ድረስ ያላቸውን ሜዎችና ፓርቲ ነው – ይህንን ደግሞ በተግባር ባለፉት አስርተ ዓመታት ተመልክቷል።

አገር የምታድገው፣ የምትለወጠው እንደት ባለ አመራርና ፓርቲ እንደሆነ ተረድቷል። ይህንኑ ለማስቀጠልም ፍላጎቱን ገልጿል። የ2005ቱ ምርጫ ዕድገቱን በማስቀጠል የተጀመሩ ሰፋፊና ከፍተኛ ፕሮጀክቶች በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ ባለው አቅም ላይ የሚወሰን ይሆናል።

የኢትዮጵያ ህዝብ በሚቀጥሉት ዓመታት መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ሊያሰልፈው የሚችለውን ጉዞ ጀምሯል ከወጠቱም ተጠቃሚ ከመሆን ባሻገር የባለቤትነት ስሜቱንም አዳብሯል። የህዳሴው ግድብ ለዚህ ሚጋገጫ ነው።

በኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ በአጭር ጊዜ ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ ያልታሰበው ይህ ግድብ ራዕይ ባለው መሪና ራዕዩን በተግባር ላይ በሚያውለው ፓርቲና ህዝብ መሪት ሲጀምር የተማማው ራሱንና ራሱን ብቻ ነው።

የህዳሴው ግድብ የአንድነታችንና የሀገር ፍቅር ማለጫችን፤ ደህነትን ታሪክ አድርገን ለማዛዝ ለጀመርነው ጉዞ ቋሚ ማገራችን በሚለት ነው። በእስካሁኑ ጉዞ ህዝብና መንግስት ያቀዱትን አሳክተዋል፡፡ እንደ አንድ ሰው በመቆም የጠለትንና የተላላኪዎቻቸውን ፕሮፓጋንዳ አምክነዋል።

አገሪቱ ደሃ ናት ህዝቡም በክልል ተከፋፍሏል፤ አንድነት የለውም፤ አብሮ በመቆም ለትግበራው አይንቀሳቀስም ሲሉ ለነበሩ አፍራሽ ሃይላትም ገንዘቡን፣ ጉልበቱን፣ ዕወቀቱንና በምንም ሊተመን የማይችለውን ህይወቱን ለማስጠት ቃል ገብቷል፤ ቃሉንም በተግባር አውሏል፤ በዚህም ጥንካሬውን አሳይቷል፡፡

ምርጫው አንድና አንድ ነው፡፡ የህዳሴውን ግድብ በማጠናቀቅ ኢትዮጵያን ከዘመናት ጠላቶችዋ ተፅዕኖና ህዝቧን ከምጣኔ ሀብት ደህነት የማላቀቅና ያለማላቀቅ ጉዳይ ነው፡፡

ምርጫው እኛ ስልጣን ላይ ከወጣን የህዳሴውን ግድብ እናቆመዋለን በሚሉ ሃይሎችና የህዳሴው ግድብ የምጣኔ ሀብት ነፃነት ሚጋገጫ የሀገራችን ሉዓላዊነት ማለጫ ነው፡፡ ለዚህም እስከ ማስዋዕትነት ድረስ በማከፈል ዝግጁ ነን በሚሉ ኃይሎች መካከል ነው። ለዚህ ደግሞ ህዝቡ ቀድሞ አውቆ ቃል ገብቷል።

ምርጫው የተጀሚው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ወደ ተግባር ተቀይሮ ህዝባችን በብልፅግና መንገድ የጀሚውን ጉዞ አጠናክሮ መቀጠል ነው፡፡ ሁሌም በስንዴ ለማኝነትና የኒዎ ሊበራሊስቶች አገልጋይ ሆኖ እንዲቀጥል ተልዕኮ በተሰጣቸው አካላት መካከል ነው፡፡

በሁለት ዓመታት ጉዞው ተስፋ ሰጪ ወጤት የተገኘበት፣ የከተማም ሆነ የገጠሩ ህዝብ በከፍተኛ ሁኔታ የተለወጠበት፣ በአደጉ አገራት ጭምር አድናቆት የተቸረው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ትክክለኛውን ማስመር ይዟል፡፡

ምርጫው አንድና አንድ ነው፡፡ አገሪቱ ያላት ሰፊ የሰው ሀይልና ጉልበት፣ እንዲሁም መሬት ነው፡፡ ይህን ተጠቅመን የምናድግበትን ፖሊሲ ቀይሰናል፡፡

በገጠር ጉልበትን በሰፊው የሚጠቀም፣ በተሚረ አርሶ አደርና አርብቶ አደር የሚመራ፣ በመንግስት በሚቀርብ የተሻሻሉና ብቃታቸው ከፍተኛ በሆነ የእርሻ ግብዓቶች የሚታገዝ፣ አርሶ አደሩንና አርብቶ አደሩን ከጎኑ በመሆን ሌት ተቀን በሚደግፉና አቅጣጫ በሚያሳዩ፣ ልምድ በሚያካፍሉና የተቀመሩ ልምዶችን በሚያስፋፉ የግብርና ባለሙያዎች እየተረዳ የግብርናውን ምርታማነት ማሳደግ ነው፡፡ ይህም ሰፊ ትግልን ጠይቋል፡፡

ትግሉ ህዝቡን በማሳመንና በማስተባበር ለአጭር ጊዜ የግብርናውን ዘርፍ ቀይሮ የገጠሩ ህዝባችንን ለብልፅግና አገራዊ ምጣኔ ሀብታችንን ወደተሻለ ደረጃ እንዲደርስ እና ለማቅጥለውም ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት አቅጣጫ ቀይሶ፣ ዕቅድ አዘጋጅቶ እየተጓዘ ባለ መንግስትና እስካሁን የሚከተሉትን ስርዓትና የምጣኔ ሀብት ፖሊሲ በሚያውቁ አካላት መካከል ነው።

የዘመኑ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አንድና አንድ ነው፡፡ ምርጫው የከተማው ነዋሪ ህዝብ ለሀገሩ ሀብት እኩል ተጠቃሚ ሊሆን አልቻለም፤ በመሆኑም ዘርፈ ብዙ የሆነውን የከተማ ነዋሪ ችግር ሊፈታ የሚችል ፖሊሲ አዘጋጅቼ በተግባር በማዋል ውጤት አግኝቻለሁ። የከተማው ነዋሪ ስር የሰደደ ችግር የነበረውን የመኖሪያ ቤት እጥረት በዘላቂነት ለመፍታት የቤቶች ልማት ፖሊሲ በማዘጋጀት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የኮንዶሚኒየም ቤቶችን በማንባት የከተማውን ነዋሪ ከሀብት ክፍፍሉ ተጠቃሚ አድርጌያለሁ፤ በቀጣይም ግዙፍ የቤቶች ልማት ግንባታን በማፋጠን ከተማውን እፎይታ እሰጠዋለሁ። ጎን ለጎንም ተምረውም ሆነ ሳይማሩ ስራ አጥ

ሆነው በድህነት አረንቋ ወስጥ የተዘፈቁ ሴቶችንና ወጣቶችን በማደራጀት የስልጠናና የመቋቋሚያ ድጋፍ በማድረግ ከቤቶች ልማት ጋር ተሳስረው በብዙ መቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ራሳቸውን እንዲችሉ አልፈውም ወደ መካከለኛ ባለሀብትነት እንዲሸጋገሩ አብቅቻለሁ፤ የዕውቀት ሽግግር እንዲፈጠር ዜጎች በራሳቸው ስራ ፈጥረው እንዲንቀሳቀሱ ዕድሉን ፈጥሬያለሁ፡

በተጨማሪም ከበለፀጉት አገራት ልምድ በመውሰድና የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ በከተማ የሚኖሩ ስራ አጥ ዜጎች በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅተው ስራ እንዲፈጥሩ ፖሊሲ በማውጣት ወደ ተግባር ተተርጉሞ አመርቂ ውጤት እንዲመጣ ብዙ ተሰርቷል፡፡

በዚህም በሴቶችና ወጣቶች እንዲሁም በከተማው ህዝብ ዘንድ አሜኔታን በማትረፍ እንዲሁም ዜጎች ስራን ሳይመርጡ እንዲሰሩ በማበረታት አማራጭ የስራ ዕድል የሚገኝበትን አቅጣጫ አይተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ችለዋል፡፡ ዜጎች የዕለት ኑሮአቸውን ከማሸነፍ ባለፈ ጥሪት መቋጠር ችለዋል፡፡

የአፍሪካ መዲና ተብላ በምትጠራው ከተማችን ወስጥ ነዋሪዎች መውጫ መግቢያ ችግሯቸው ሬሳ በሰው ትከሻ በቅብብሎሽ እንዲያልፍ ይገደዱ ነበር፡፡ ሴቶች ወጣቶች ህፃናት ሽማግሌዎች አሮጊቶች ከቤት መውጫ አንድ ጫማ ለስራ ቦታ፣ ትምህርት ቤትና ንግድ ቦታ ለሚውሉበት ሌላ ጫማ ማያዝን ታሪክ ያደረገ ሰፊ የወስጥ ለወስጥ መንገድ ሥራ ማለትም የኮብል ስቶ ንጣፍ ትልቅ ማሳያ ነው፡፡ 7

የከተማው ነዋሪ፣ የገጠሩ አርሶ አደርና አርብቶ አደር ስራን ሳይንቁ፣ የመንግስት ተቀጣሪነትን ሳይጠብቁ ስራ ፈጥረው በማስራት፣ የቁጠባ ባህልን በማዳበር በጎ በጎ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

ከተነሳ አይቀር ስራ የሚንቁ፣ ህዝባችን ወደ ቢሮክራሲ ስራ ብቻ እንዲያስብ፣ የመንግስትና የግል ባለሀብት ተቀጣሪነትን ብቻ እንዲያልም የሚሹ አንዳንድ ኃይላት ዛሬ ምን ያስቡ ይሆን?

አሜሪካና አወሮፓ በሀብታቸው በዓለም ህዝቦች ላይ ተፅዕኖ መፍጠር የቻሉ ሀገራት ዜጎች ዛሬ ምን እየሰሩ ይሆን? በየቀኑ ትላልቅ ጎዳናዎቻቸው ስራ አጥ በሆኑ ዜጎቻቸው ሲጥለቀለቁ ሀብታም ናቸውና ፋብሪካ እየከፈቱ የመንግስት ተቋማትን በማስፋፋት ተቀጣሪ እንዲሆኑ ለምን አላደረጓቸውም?

ለማሆኑ በበለፀጉ ሀገራት ተሰደው የሚኖሩ ሀኪሞቻችንና ፕሮፌሰሮቻችን ከጥቂቶች በስተቀር ምን እየሰሩ ይሆን የሚኖሩት። የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በስራ ክቡርነት ስለሚያምን ምንም ሰሩ ምንም ራሳቸውን እስከቻሉ፣ ወገኖቻቸውን እስከረዱ ድረስ ብዙ ሊስገርም አይችል ይሆናል፡፡

ራሳቸው እያረረባቸው ዜጎቻችን በጥቃቅንና አነስተኛ ዘርፍ ተደራጅተው ስራ በመፍጠር ራሳቸውን ሲችሉ ለምን ዝቅተኛሥራ ላይ ትሳተፋላችሁ ለሚሉ አካላት እባካችሁ አንዱ ጣታችሁን ወደ ኢትዮጵያ ስትቀስሩ አራቱ ወደ እናንተ ይቀሰራልና መጀመሪያ ራሳችሁን ተመልከቱ፡፡ አማራጭ ሀሳብ ካላችሁ በራሳችሁ ላይ ሞክሩ፡፡ ወጤታማ ከሆነ ከእነ ካፒታሉ ወደ እኛ ላኩ እንላለን።

ታዲያ ምርጫችን የሚሆነው ተግባር ወጤት ለወጥ፣ ብልፅግና ባመጡልን ፖሊሲና ድንማን ወሮደትን ጥቃትን ሊያላብሱን በሚፈልጉ ኃይላት መካከል ነው። ለዚህ ደግሞ ነቅተናል፤ አወቀናል፤ የሚበጀንን ለይተናል፡፡

ምርጫውን በንቃትና በቁርጠኝነት እየተጠበበቅን ነው፡፡ ለአፍራሽ ፕሮፓጋንዳ ጆሮአችንን አንሰጥም፡፡ ወቅቱ ሲደርስ የምርጫ ጣቢያዎችን በማንቀሳቀስ ለዓለም ህዝብ ብስለታችንን፣ አንድነታችንን በማሳየት የኢትዮጵያን ገፅታ ከአሁኑ በበለጠ እንቀይራለን። እስከዚያው ቸር እንሰንብት።